# <u>የባለሀገሩ ልጅ</u>

ከእኔ ዓለም

የባለሀገሩ ልጅ ቂጣ መቀንቱ
ማተብ ግዛ ቢሉት  ነገረ ለናቱ

ለናቱ መንገሩስ በርግጥም ባልከፋ
የሀገር ምስጥሮች ተወሩ በይፋ

ምስጥርና እውነት አይ አካሄዳቸው
አደባባይ ወጡ እኔስ ፈራኃቸው።

- የባለሀገሩ ልጅ መካሪ የሌለው
  ቂጣውን አንግቶ ማተቡን ሰወረው

-

  ያቺ ኩርማን ቂጣ እንዲህ ፈተነችው
  ማተቡን አስጥላ ክብሩን ወረሰችው
  ባደባባይ ወጥታ አንገላጀጀችው

በድህነቴ ላይ ማተቤ እንዳትላላ
እኔስ አልባልም ጥቅመኛ ደላላ
ከዳተኛ ሆኜ የታሪክ አተላ

- ያ ድርብ ማተብ በሶስት ተገመደ
  በቀስተ ዳመና በደም ተዋሕደ

ይኸ ህብረ ቀለም ጠብቆ ተጎንጉኖ
ማንነቴን አወቅሁ ማተብ ሀገር ሆኖ ።

ነሐሴ 6/ 2004